Washington State Department of Labor & Industries

# ጥያቄዎች እና መልሶች፡ የHELSA እና የPPE አጠቃቀም ሪፖርት ማድረግ እና ማሳወቂያ መስፈርቶች

ለመጨረሻ የተሻሻለው በኤፕሪል 29፣ 2022

**ዳራ**

የዋሽንግተን ስቴት ሁለት የስራ ቦታ የደህንነት እና ጤና ህጎችን፣ የህዝብ ጤና ድንገተኛ ሪፖርት ማቅረብ እና ለኢንፌክሽን እና ተላላፊ በሽታዎች የማሳወቂያ መስፈርቶች፣ WAC 296-62-600 እና የህዝብ ጤና ድንገተኛ የበጎ ፈቃደኝነት የግል መከላከያ መሳሪያዎች አጠቃቀም፣ WAC 296-62-601 አሻሽሏል። በመጀመሪያ በኦገስት 10፣ 2021 ከፀደቀ በኋላ በኤፕሪል 2022 ውስጥ የተሻሻለው፣ እነዚህ ህጎች፣ የአሁኑን COVID-19 ወረርሽኝ ጨምሮ፣ የኢንፌክሽን ወይም ተላላፊ በሽታን የሚያካትቱ የህዝብ ጤና ድንገተኛ አደጋዎች በታወጁ ወቅት የሚተገበር ነው። እነሱም ህግ እንዲሆኑ በመንግስት የተፈረሙ የህግ መስፈርቶችን ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ ጄይ ኢንስሊ (Jay Inslee)፡

- የአሰሪ ሪፖርት ማድረግ እና የማሳወቂያ መስፈርቶች የሚመነጩ፣ አሁን በRCW 49.17.062 እና RCW 49.17.064 ላይ ከሚገኙት ከጤና ድንገተኛ የጉልበት ደረጃዎች ህግ ወይም "HELSA" ነው፡፡
- በ RCW 49.17.485 ላይ የተመሠረተ፣ በሕዝብ ጤና ድንገተኛ አደጋ ወቅት የፊት ጭንብል እና ሌሎች የግል መከላከያ መሳሪያዎችን (PPE) በፈቃደኝነት መጠቀም ለቀጣሪዎች የሚያስፈልጉ መስፈርቶች ናቸው

በኤፕሪል 2022 የተሻሻለው የአደጋ ጊዜ ህግ ለሁሉምን የቀጣሪዎች እና የጤና እንክብካቤ ተቋማት መስፈርቶችን ያካትታል (በRCW 9A.50.010 እንደተገለጸው)፡-

- በሥራ ቦታ ወይም በሥራ ጣቢያ ከ50 በላይ የተሸፈኑ ሠራተኞች ያሏቸው ቀጣሪዎች፣ የኢንፌክሽን ወይም የተላላፊ በሽታዎችን ወረርሽኝ ለ L&I ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፤
- የጤና እንክብካቤ የሌላቸው ቀጣሪዎች በአንድ የስራ ቀን ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ተጋላጭነቶችን፣ በጽሁፍ ለሰራተኞቻቸው እንዲሁም ለሰራተኛ ማህበራት ተወካይ (ካለ) ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ሰራተኞች እና ኮንትራክተሮች በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የግል መከላከያ መሳሪያዎችን እንዲጠቀሙ መፍቀድ አለባቸው፡፡
- የጤና አጠባበቅ ተቋማት አሰሪዎች ማንኛውንም በኢንፌክሽን እና በተላላፊ በሽታ ከፍተኛ- አደጋ ተጋላጭነት የሚታወቅ ወይም የሚጠረጠርን ሰራተኛ በ24 ሰዓት ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው።
    - ከሰራተኛ ፈቃድ ጋር፣ ማሳወቂያው በ24 ሰዓታት ውስጥ ለሰራተኛው ማህበር ተወካይ (ካለ)መላክ አለበት።

የሚከተሉት ጥያቄዎች እና መልሶችም አዲሱን ህግጋቶች እንዲረዱት እና እንዲያከብሩ ሊረዳዎት ይችላል፣ WAC 296-62-600 እና WAC 296-62-601 ፣ https://lni.wa.gov/safety-health/safety-rules/rulemaking-stakeholder-information/HELSA-docs/HELSA-emergency-rule-language-Amharic.pdf ላይ ይገኛሉ።

## በሕዝብ ጤና ድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ወረርሽኞችን ለ L&I ሪፖርት ማድረግ

### ቀጣሪዎች በአሁኑ COVID-19 ወረርሽኝ ወቅት ወረርሽኞችን ለ L&I ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል?

አዎ። 50 ወይም ከዚያ በላይ የተሸፈኑ ሰራተኞች ያሏቸው አሰሪዎች፣ በዋሽንግተን ስቴት ውስጥ ለስራ ቦታዎች ወይም የስራ ጣቢያዎች COVID-19 ወረርሽኝ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። ይህም በRCW 9A.50.010 በተገለጸው መሰረት፣ በጤና እንክብካቤ ተቋማት ውስጥ ያሉ የስራ ቦታዎችን ወይም የስራ ጣቢያዎችን ይጨምራል። መስፈርቶቹም የታወጀው የህዝብ ጤና ድንገተኛ አደጋ እስኪያበቃ ድረስ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

እነዚህ የሪፖርት ማቅረቢያ መስፈርቶችም በዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዝዳንት ወይም በዋሽንግተን ግዛት ገዥ በታወጀው ወይም በታዘዙት መሠረት፣ ወደ ፊት ለሚከሰቱት የእንፌክሽ ወይም ተላላፊ በሽታን በሚያካትቱ ወረርሽኞች ወይም ሌሎች የህዝብ ጤና ድንገተኛ አደጋዎች ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

### ወረርሽኝ ምንድነው?

በአጠቃላይ፣ ወረርሽኝ ማለት በአንድ የስራ ቦታ ወይም የስራ ጣቢያ ላይ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚከሰቱ የኢንፌክሽኖች ስብስብ ናቸው።

ይህ ደንብ በተለይ COVID-19 ወረርሽኝ፣ አሥር ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሠራተኞች የተረጋገጠ COVID-19 ምርመራ ኢንፌክሽኖች በተከሰቱት የምርመራ መሰብሰቢያ ቀናት ላይ ስራ ላይ ይውላል:-

- በ14 ተከታታይ የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ማንኛውም ሁለት (ወይም ከዚያ በላይ) የተገኘባቸው ሰዎች ከተከሰተበት ጊዜ የሚጀምረው እና አዲስ ኢንፌክሽን ሳይከሰት 28 ተከታታይ የቀን መቁጠሪያ ቀናት ካለፉ ያበቃል፣ ወይም
- በማንኛውም የዋሽንግተን ስቴት የጤና መምሪያ ወይም የአካባቢ ጤና ሥልጣን፣ በስራ ቦታቸው ወይም በስራ ጣቢያቸው COVID-19 ወረርሽኝ እንዳለ ለአሰሪው ባሳወቀበት ጊዜ።

### ሽፋን ያለው ሰራተኛ ማንነው?

ሽፋን ያላቸው ሰራተኞች በየሰዓት፣ በደመወዝ፣ በጉልበት፣ በአስተዳደር፣ የትርፍ ሰዓት እና ወቅታዊ ሰራተኞች ናቸው፣ እና ማንኛውም ከጊዜያዊ የእርዳታ አገልግሎት የተቀጠረ ሰራተኛ፣ አገልግሎት አከራይ ሰራተኛ ወይም በየቀኑ የሰራተኛ አቅርቦት አገልግሎት የሚቆጣጠር ከሆነ አገልግሎት አቅራቢ ሰራተኛ (በWAC-296-27-02103, https://apps.leg.wa.gov/WAC/default.aspx?cite=296-27-02103) መሰረት::

### ቀጣሪዎች ወረርሽኞችን እንዴት ሪፖርት እንደሚያደርጋሉ እና ምን ያህል ጊዜ ሪፖርት ለማድረግ አላቸው?

አሠሪው አንዴ አሥር ወይም ከዚያ በላይ የታመሙ ሰዎች በሥራ ቦታ ወይም በሥራ ጣቢያ መከሰታቸውን ካወቀ በኋላ፣ አሠሪው ለ L&I የሥራ ደህንነት እና ጤና ክፍል (DOSH) በ1-800-4BE-SAFE (ወይም 1-800-423-7233) ላይ በመደወል እና "የሞት አደጋን፣ ሆስፒታል መተኛትን፣ መቆረጥን ወይም የዓይን መጥፋትን ሪፖርት ማድረግ" የሚለውን አማራጭ በመከተል ስለወረርሽኙን ለማሳወቅ 24 ሰዓት አለው።

ለDOSH ሪፖርት በሚያደርጉበት ጊዜ፣ **የየትኛውንም ሰራተኛ ስም(ዎችን) ወይም የግል መለያ መረጃን አያካትቱ፡፡**

### ቀጣሪዎች ወረርሽኝ በሚከሰትበት ጊዜ ከአንድ ጊዜ በላይ ሪፖርት ማድረግ አለባቸውን?

ቀጣሪው አንዴ ወረርሽኙን ሪፖርት ካደረገ በኋላ፣ ምንም እንኳን ተጨማሪ ህመም ቢከሰቱም፣ ለዚያ ወረርሽኝ ተጨማሪ ሪፖርት ማድረግ አያስፈልገውም።

አንዳንድ የስራ ቦታዎች ምንም አዲስ ህመም ሳይከሰተ 28 ቀናት ካለፉ በኋላ አዲስ ወረርሽኝ ሊያጋጥማቸው ይችላል፣ ይህ ሁኔታ ከተከሰተ፣ አሰሪው አዲሱን ወረርሽኝ ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል።

## የተጋላጭነት ማስታወቂያ (ሁሉም አሰሪዎች)

### ቀጣሪዎች በአሁኑ ወረርሽኝ ወቅት COVID-19 መጋለጥን ለሰራተኞቻቸው ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል

አዎ። የሰራተኛ ማስታወቂያ መስፈርቶች አሁን COVID-19 ህመሞች ተግባራዊ ናቸው እና የታወጀው የህዝብ ጤና ድንገተኛ አደጋ እስኪያበቃ ድረስ ተፈጻሚ ይሆናሉ። የሰራተኛ ማሳወቂያ መስፈርቶች በWAC 296-62-600 ለተሸፈኑ ቀጣሪዎች በሙሉ ይኖራል።

እነዚህ መስፈርቶች በማንኛውም ወደፊት በዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዝዳንት ወይም በዋሽንግተን ግዛት ገዥ በታወጀው ወይም በታዘዙት ወረርሽኞች ወይም ሌሎች እንፌክሽን ወይም ተላላፊ በሽታዎችን በሚያካትቱ የህዝብ ጤና ድንገተኛ ሁኔታዎች ተግባራዊ ይሆናሉ።

### ብቁ የሆነ ግለሰብ ማንነው?

ብቁ የሆነ ግለሰብ ማለት COVID-19 ተመርምሮ ፖዘትቭ የሆነ፣ በጤና እንክብካቤ አቅራቢ COVID-19 የተመርመረ፣ ለብቻው እንዲገለል የታዘዘ ወይም በሕዝብ ጤና ድንገተኛ አደጋ ምክንያት በእንፌክሽን ወይም ተላላፊ በሽታ የሞተ ሰው ነው።

### የጤና እንክብካቤ ተቋማት በማስታወቂያ መስፈርቶች ተሸፍነዋልን?

አዎን፣ በኤፕሪል 2022 የወጣው WAC 296-62-600 በRCW 9A.50.010 እንደተገለጸው፣ ለጤና እንክብካቤ ተቋማት የማሳወቂያ መስፈርቶችን ያካትታል።

### የጤና እንክብካቤ የሌላቸው ቀጣሪዎች ማሳወቂያዎች ከጤና እንክብካቤ ተቋማት ጋር ተመሳሳይ ናቸው?

አይ፡፡ በአሰሪው ለሰራተኛው(ቶች) የሚሰጠው ማስታወቂያ በRCW 9A.50.010 በተገለጸው መሰረት፣ የጤና እንክብካቤ ተቋሙ ትርጉም ይወሰናል። የጤና እንክብካቤ ተቋማት እና የጤና እንክብካቤ የሌላቸው ቀጣሪዎች፣ የማሳወቂያ ቀስቅሴዎችን ጨምሮ፣ የተለያዩ መስፈርቶች አሏቸው። ለምሳሌ፡-

- የጤና አጠባበቅ ተቋም ያልሆነ ቀጣሪ ሠራተኛ ሊጋለጥ እንደሚችል ማስታወቂያ ከደረሰው፣ ቀጣሪው በተላላፊው ጊዜ ውስጥ ሁሉንም ሰራተኞች ማሳወቅ አለበት። እነሱም በአንድ (1) የስራ ቀን ውስጥ ለእነዚያ ግለሰቦች ሊጋለጡ እንደሚችሉ ማስታወቂያ መስጠት አለባቸው።
- የጤና አጠባበቅ ተቋም አሰሪዎችም ሰራተኛው የሚታወቅ ወይም የተጠረጠረ ከፍተኛ የሆነ ለኢንፌክሽን ወይም ተላላፊ በሽታ የመጋለጥ አደጋ በሚኖርበት ወቅት፣ ለሰራተኞች ማሳወቅ አለባቸው። አሠሪው ለሠራተኞች ለኢንፌክሽን ወይም ተላላፊ በሽታ ተጋላጭነትን ከፍተኛ መሆኑን ለማሳወቅ 24 ሰዓት አለው።

### 50 ወይም ከዚያ ያነሱ ሰራተኞች ካሉኝስ?

ከላይ እንደተገለፀው፣ በአንድ የተወሰነ የስራ ቦታ ላይ 50 ወይም ከዚያ ያነሰ ሽፋን ያላቸው ሰራተኞች ያሏቸው ቀጣሪዎች ወረርሽኞችን ለL&I ሪፖርት ማድረግ የለባቸውም። ሆኖም ግን አሁንም ሰራተኞችን እንዲያሳውቁ ይጠበቃሉ።

## ሊከሰት የሚችል ተጋላጭነት (የጤና አጠባበቅ ቀጣሪዎች -ያልሆኑ) ሰራተኞችን ማሳወቅ

### የጤና እንክብካቤ ላልሆኑ ቀጣሪዎች የማሳወቂያ መስፈርት የሚያነሳሱ ምንድን ናቸው?

በእያንዳንዱ ቀጣሪ የመጋለጥ እድልን ማሳወቂያ በደረሰ ቁጥር የማሳወቂያ መስፈርቱ ይቀሰቀሳል:-

- በአሰሪው የፈተና ፕሮቶኮል አማካይነት፣ አንድ ሠራተኛ ብቁ የሆነ ግለሰብ ነው፣ ወይም
- ከሰራተኛ (ወይም በአደጋ ጊዜ ተጠሪያቸው) ሰራተኛው ብቁ የሆነ ግለሰብ ነው፣ ወይም
- ከህክምና አቅራቢ ወይም ከህዝባዊ ጤና ባለስልጣን ሰራተኛው በስራ ቦታው ላይ የተጋለጠ ከሆነ ብቃት ያለው ግለሰብ ነው።

### የጤና እንክብካቤ ያልሆኑ ቀጣሪዎች ለማን ማሳወቅ አለባቸው?

አሠሪው እንፌክሽን ወይም ተላላፊ በሽታ ሊያዙ እንሚችሉት እንደ ብቁ ግለሰብ በተመሳሳይ ቀን(ናት) በተመሳሳይ የሥራ ቦታ ግቢ ውስጥ የነበሩትን ሁሉንም የተሸፈኑ ሰራተኞች በሙሉ ማሳወቅ አለበት። COVID-19፣ ብቁ የሆነ ግለሰብ እንፌክሽን ወይም ተላላፊ በሽታ ሊያስከዝ ይችላል:-

- የህመም ምልክክት ያለው ከሆነ፣ ቢያንስ መታመም ከመሰማቱ ከሁለት ቀናት በፊት፣ ወይም
- የህመም ምልክት የሌለው ከሆነ፣ ቢያንስ ከምርመራ ናሙና መሰብሰብ 2 ቀናት በፊት፣ እና
- ራሳቸውን እስኪያ ገሉ ወይም የስራ ቦታን እስከሚለቁ ድረስ፡፡

### የጤና እንክብካቤ ያልሆኑ ቀጣሪዎች ለማንኛው ሰው የጽሁፍ ማሳሰቢያ መስጠት አለባቸው?

አዎ፣ ቀጣሪዎች ለሚከተሉት የጽሁፍ ማሳሰቢያ መስጠት አለባቸው፡-

- በሰራተኛ የተፈቀደለት የሰራተኛ ማኅበር ተወካይ(ዎች) የማንኛውም የተሸፈነ ሰራተኛ ማስታወቂያ ይቀበላል።
- ጊዜያዊ የእርዳታ አገልግሎት፣ ሰራተኛ የአከራየው አገልግሎት፣ ወይም የሰራተኛ አቅርቦት አገልግሎት አሰሪ ማንኛውም ሰራተኛ ማሳወቂያ ይቀበላል።

### የጤና እንክብካቤ ያልሆኑ ቀጣሪዎች እንዴት ነው ማሳወቂያ መስጠት አለባቸው?

አሰሪው ከቅጥር ጋር የተያያዘ መረጃን ለማስተላለፍ በተለምዶ በሚገለገልበት መንገድ የፅሁፍ ማስታወቂያን መስጠት አለበት። ይህ የሚያጠቃልለው ለግል አገልግሎት ብቻ የተወሰነ፣ እንደ ኢሜል ወይም የፅሑፍ መልእክት ብቻ አይደለም - ማሳወቂያው በሠራተኛው በአንድ የሥራ ቀን ውስጥ ሊደርሰው በምክንያታዊነት የሚጠበቅ ተደርጎ ይታሰባል።

የፅሁፍ ማስታወቂያው በእንግሊዝኛ እና አብዛኞዎቹ ሰራተኞች በሚረዱት ቋንቋ መሆን አለበት። ይህም ለሰራተኛ ማህበራት ተወካዮች እና አሰሪዎች በሚሰጡ የፅሁፍ ማሳሰቢያዎች ላይም ይሠራል።

### የጤና እንክብካቤ ባልሆኑ ተቋማት ውስጥ በአሰሪዎች የሚቀርቡ ማሳወቂያዎች የሰራተኞችን ስም ሊያካትቱ ይችላሉ?

**አይ፡፡**በደንቡ መሰረት፣ ሽፋን ለተሰጣቸው ሰራተኞችየፅሁፍ ማሳሰቢያዎች **የትኛውንም የሰራተኛ ስም(ዎች) ወይም የግል መረጃዎችን ማካተት የለባቸውም።**

ማስታወቂያዎችም መረጃው የተሸፈነውን ሠራተኛ ማንነት ለመለየት የሚመራ እስካልሆነ ድረስ፣ እንደ ሚሠራበት ፕሮግራም ወይም አካባቢ ያሉ መረጃዎችን ሊያካትቱ ይችሉ ይሆናል።

### የጤና እንክብካቤ ያልሆነ ቀጣሪ ሰራተኞችን፣ ማህበራትን እና ሌሎች አሰሪዎችን የሚያሳውቀው ለምን ያህል ጊዜ?

ለሰራተኞች፣ ለማህበር ተወካይ እና ለሌሎች ቀጣሪዎች ተጋላጭ(ዎች) የፅሁፍ ማስታወቂያ ለማቅረብ አንድ የስራ ቀን።

## የከፍተኛ ስጋት ተጋላጭነት (የጤና እንክብካቤ ተቋማት) ሰራተኞችን ማሳወቅ

### የጤና እንክብካቤ ተቋማት ምንድነው?

የጤና እንክብካቤ ተቋማት ማለት ሆስፒታል፣ ክሊኒክ፣ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ቢሮ፣ የጤና ጥበቃ ድርጅት፣ የምርመራ ወይም ህክምና ማዕከል፣ ኒውሮሳይካትሪ ወይም የአእምሮ ጤና ተቋም፣ ሆስፒስ ወይም የነርሲንግ ቤትን ከ RCW 9A.50.010 ጨምሮ ለታካሚዎች በቀጥታ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው፡- መግለጫዎች።

### የጤና እንክብካቤ ተቋማት ሽፋን ያላቸውን ሰራተኞች እንዴት እና መቼ ማሳወቅ አለባቸው?

የጤና እንክብካቤ ተቋማት ማንኛውንም የታወቀ ወይም የተጠረጠረ COVID-19 ከፍተኛ ተጋላጭነት ያለው ሰራተኛን በ24 ሰዓት ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው። ከሰራተኛ ፈቃድ ጋር፣ አሰሪው የታወቀ ወይም የተጠረጠረበትን COVID-19 ከፍተኛ ተጋላጭነት ያለውን ለሰራተኛው ሁኔታ በ24 ሰአት ውስጥ ለህብረቱ ተወካይ ማሳወቅ አለበት።

### በጤና እንክብካቤ ውስጥ ከፍተኛ ተጋላጭነት ምንድነው?

ለከፍተኛ ተጋላጭነት ማለት ብቃት ያለው የመተንፈሻ መሣሪያ እና ሌሎች አስፈላጊ የግል መከላከያ መሣሪያዎች ከሌሉ ከሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ መሆን ማለት ነው፡

- ብቁ የሆነ ግለሰብ በስድስት ጫማ ርቀት ውስጥ በአጠቃላይ ለ15 ደቂቃ ወይም በ24-ሰአት ጊዜ ውስጥ ከዚያ በላይ ጊዜ ብቁ የሆነ ግለሰብ ሊተላለፍበት በሚችልበት ጊዜ ነው።
- የትንፋሽ የማመንጨት (aerosol-generating)ሂደትን እንደ ሚከታተል ሰው ብቁ የሆነ ግለሰብ በተመሳሳይ ክፍል ውስጥ። የትንፋሽ የማመንጨት ሂደር ዝርዝርን በ https://www.doh.wa.gov/Portals/1/Documents/1600/coronavirus/COVID19InfectionControlForAerosolGeneratingProcedures.pdf. ላይ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡
- የማጽዳቱ ጊዜ ከማብቃቱ በፊት፣ ብቁ የሆነ ግለሰብ የአየር ማራዘሚያ ሂደትን ባደረገበት ክፍል ውስጥ ከሆነ።

### ለጤና አጠባበቅ ተቋማት የሚተላለፉበት ጊዜ ስንት ነው?

COVID-19 ብቁ የሆነ ግለሰብ ከመታመሙ/የህመም ምልክቶች ከመታየቱ ከሁለት ቀናት በፊት (ወይም የህምም ምልት ለማያሳዩ ሰዎች፣ የምርመራ ናሙና ከመሰብሰቡ ከሁለት ቀን በፊት)፣ ብቁ የሆነው ግለሰብ እስከሚሄድ እና/ወይም ተነጥሎ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ፣ የፈለገ ረጅም ቢሆንም፤ ከሥራ ቦታው ወይም በበሽታ መቆጣጠሪያ ማዕከል (CDC) ወደ ሥራ የመመለሻ መመዘኛዎች በተለመደው የሰራተኞች ፕሮቶኮል መሰረት እስከሚያልፍ ድረስ፣ እንፌክሽን ወይም በሽታ አስተላላፊ ሊሆን ይችላል። ለተጨማሪ መረጃ ይመልከቱ https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/hcp/mitigating-staff-shortages.html

### የክፍል ማፅጃ ስንት ነው?

የማጽዳት ጊዜ ማለት በ 99.9 በመቶ የማስወገጃ ቅልጥፍና በሲዲሲ (CDC) መመሪያዎች መሰረት የትንፋሽ ማመንጫን ከክፍል ውስጥ ለማስወገድ የሚፈጀው ጊዜ ማለት ነው። https://www.cdc.gov/infectioncontrol/guidelines/environmental/appendix/air.html#tableb1 ይመልከቱ)። ይህም ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ተከትሎ ከሶስት ሰዓት ያልበለጠ ነው። በ DOH ክሊኒካዊ ፋሲሊቲ መስፈርቶች (በሰዓት ስድስት የአየር ልውውጦች) በተገነቡ ክሊኒካዊ ቦታዎች አንድ ሰአት በቂ ነው እንዲሁም በአየር ወለድ ኢንፌክሽን ማግለል ክፍል (AIIR) ውስጥ 15 ደቂቃ በቂ ነው።

### አሰሪዎች በጤና እንክብካቤ ተቋማት የሚቀርቡት ማሳወቂያዎች የሰራተኞችን ስም ሊያካትቱ ይችላሉ?

በአሜሪካ የአካል ጉዳተኞች ህግ (ADA) መሰረት የግለሰብ ሰራተኞች COVID-19 ሁኔታ ሚስጥራዊ መሆን አለበት። ለተጨማሪ መረጃ፣ ከዩናይትድ ስቴትስ እኩል የስራ እድል ኮሚሽን የተገኘውን መረጃ ይመልከቱ፡ https://www.eeoc.gov/wysk/what-you-should-know-about-covid-19-and-ada-rehabilitation-act-and-other-eeo-laws.

## COVID-19ን ይፋ ማድረግ

### WAC 296-62-600 የማንኛውንም ሰራተኛ የጤና ሁኔታ ወይም ለቀጣሪያቸው ምርመራን መግለጽ የሚከለክለው?

ከ RCW 49.17.062 ጋር በመስማማት፣ ደንቡ የማንኛውንም ሠራተኛ የሕክምና ምርመራ ወይም ሁኔታ ይፋ ማድረግን አይከለክልም፡፡ ይህ ለሁለቱም የጤና እንክብካቤ ተቋማት እና የጤና እንክብካቤ ላልሆኑ ቀጣሪዎች ይሠራል።

### WAC 296-62-600 የማንኛውንም ሰራተኛ የጤና ሁኔታ ወይም የቀጣሪያቸው ምርመራ ይፋ ለማድረግ አዲስ መስፈርቶችን ይፈጥራል?

ከ RCW 49.17.062 ጋር በመስማማት፣ ደንቡ የማንኛውንም የሰራተኛ የሕክምና ምርመራ ወይም ሁኔታ ይፋ ለማድረግ ምንም አዲስ መስፈርቶችን አይፈጥርም። ይህም ለሁለቱም የጤና እንክብካቤ እና የጤና እንክብካቤ ያልሆኑ ቀጣሪዎችን ይሰራል።

### ቀጣሪዎች ሰራተኞቻቸውን COVID-19 ታመው ከሆነ ወይም ተመርምረው እንደሆን መጠየቅ ይችላሉ?

DOSH ቀጣሪዎች ለምሳሌ COVID-19 የተያዙ ሰራተኞችን በቤት እንዲቆዩ ማድረግ፤ COVID-19 ስርጭትን በስራ ስፍራ እንዲቆጣጠሩ መጠበቁን ይቀጥላል፡፡ ደንቡ ህጋዊ የሆነ አሰሪ ለሰራተኛው COVID-19 ጋር በተገናኘ ጥያቄዎችን መጠየቅን አይከለክልም። ስለዚህ እና ሌሎች የእኩል እድል የህግ ጥያቄዎችን በተመለከተ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ ቀጣሪዎች እና ሰራተኞች የዩናይትድ ስቴትስ የእኩል የስራ እድል ኮሚሽን የቴክኒክ ድጋፍ ሰነድን በ፡ https://www.eeoc.gov/wysk/what-you-should-know-about-covid-19-and-ada-rehabilitation-act-and-other-eeo-laws ላይ ማማከር አለባቸው።

## ቅሬታዎች

### ሰራተኞች ማስታወቂያዎችን በሰዓቱ እና WAC 296-62-600 በሚጠይቀው መሰረት እየተቀበሉ እንዳልሆነ ካመነኩኝ እንዴት ቅሬታ ላቅርብ?

በ1-800-4BE-SAFE (ወይም 1-800-423-7233) ላይ ለ DOSH መደወል ይችላሉ፡፡ ወይም በ https://www.lni.wa.gov/workers-rights/workplace-complaints/safety-complaints ላይ የሚገኘውን የ DOSHን የቅሬታ የቅፅን መሙላት ይችላሉ፡፡

## የግል መከላከያ መሳሪያዎችን (PPE) በፈቃደኝነት መጠቀም

### በፈቃደኝነት የPPE አጠቃቀም ምንድን ነው?

በፈቃደኝነት መጠቀም የሚያመለክተው፣ በዋሽንግተን የኢንዱስትሪ ደህንነት እና ጤና ህግ (WISHA፣ ምዕራፍ 49.17 RCW) ወይም እንፌክሽንን እና ተላላፊ በሽታን በተመለከተ በሕዝብ ጤና ድንገተኛ አደጋ ወቅት በአሠሪው በማይፈጠየቅበት ጊዜ፣ ሠራተኛ ወይም የሥራ ተቋራጭ በስራ ቦታ ላይ የፊት ጭንብል ወይም ሌላ PPE መጠቀምን አማራጭ ያመለክታል፡፡

ለምሳሌ፣ የበለጠ ተከላካይ የፊት ጭምብል (መተንፈሻ)እንደ N95 ያሉትን PPE በፈቃደኝነት ለመጠቀም የሚፈለግ ሰራተኛ ወይም ኮንትራክተር የመከላከል ደረጃቸውን ማሻሻል ሲፈልጉ በፈቃደኝነት መጠቀም ሊከሰት ይችላል፡፡

### አንድ ሰው PPEን በፈቃደኝነት ለመጠቀም ከፈለገ ቀጣሪ ምን ማድረግ አለበት?

አሰሪዎች ማንኛውምን ሰራተኛ ወይም ስራ ተቋራጭ (ሙሉ በሙሉ የተከተቡ ወይም ያልተከተቡትንም) PPEን በፈቃደኝነት እንዲጠቀሙ መፍቀድ አለባቸው፣ ነገር ግን አሰሪው አጠቃቀሙን የሚከተሉትን መሆን የሌለበትን ከወሰነ በኋላ ብቻ:-

- የደህንነት ወይም የጤና አደጋ መፍጠር፣ ወይም
- በአሰሪው የደህንነት መስፈርቶች ላይ ጣልቃ መግባት፣ ወይም
- በሌሎች የሚመለከታቸው የጤና እና የደህንነት ደንቦች ከተገለጹት የPPE መስፈርቶች ጋር መጋጨት።

### አሠሪዎች በፈቃደኝነት ጥቅም ላይ ለዋለ PPE መክፈል አለባቸው?

አይ፣ አሰሪዎች ለሚፈለገው PPE ብቻ መክፈል አለባቸው፡፡

### ሰራተኞች PPEን በፈቃደኝነት እንዲጠቀሙ በWAC 296-62-601 መሰረት እንደማይፈቀድላቸው ካመንኩ እንዴት ቅሬታ ላቅርብ?

በ1-800-4BE-SAFE (ወይም 1-800-423-7233) ላይ ለ DOSH መደወል ይችላሉ፡፡ ወይም በ https://www.lni.wa.gov/workers-rights/workplace-complaints/safety-complaints ላይ የሚገኘውን የ DOSHን የቅሬታ የቅፅን መሙላት ይችላሉ፡፡

---

*ስለኤጀንሲ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶችን በተመለከተ በቋንቋዎ መረጃ ከፈለጉ በ1-800-547-8367 ላይ የዋሽንግተን እስቴት የሰራተኛ እና ኢንዱስትሪዎች (Labor & Industries) መምሪያን ያግኙ፡፡ ይህ አገልግሎት በነፃ ነው፡፡*

*ከተጠየቀ፣ የአካል ጉዳት ላላቸው በሚሆን መልክ ይገኛል፡፡ በ1-800-547-8367 ይደውሉ፡፡ ለTDD ተጠቃሚዎች 711 ይደውሉ፡፡ የሰራተኞችና ኢንዱስትሪ (L&I) እኩል የስራ እድል ያቀርባል፡፡*